# በአገራችን ለሚኖሩ የራስ-ተፈሪያውያን ማህበረሰብ አባላት የኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆኑ የውጭ አገር ዜጎች የተሰጡ መብቶች የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 21/2009

ሰኔ 2009 ዓ.ም

ውጭ ጉዳይ ማኒስቴር

አዲስ አበባ

## በአገራችን ለሚኖሩ የራስ-ተፈሪያውያን ማህበረሰብ አባላት የኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆኑ የውጭ አገር ዜጎች የተሰጡ መብቶች የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር.21/2009

በአገራችን ለረጅም ዓመታት የኖሩ የራስተፈሪያን ማሕበረሰብ አባላት እና ቤተሰቦቻቸው ከአገራችን ጋር ያላቸውን ታሪካዊ ትስስር ማጠናከር በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀጽ 8(8) በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ የውጭ አገር ዜጎች በልዩ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የተሰጡ መብቶችንና ጥቅሞችን ሊያገኙ እንደሚችሉ በመደንገጉ ይህ መመሪያ ወጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በአገራችን ለረጅም ጊዜ የኖሩ የራስ-ተፈሪያውያን ማህበረሰብ አባላት የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር.21 /2009 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

2.1. ማህበረሰብ ማለት በአገራችን ለረጅም ዓመታት በመኖር ላይ የሚገኙ የራስ-ተፈሪያን ማህበረሰብ አባላት ናቸው::

2.2. ሚኒስቴር ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው::

2.3. አገልግሎት ማለት ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ነው::

2.4. ኢሚግሬሽን ማለት የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ነው::

2.5. አዋጅ ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 ነው::

2.6. ደንብ ማለት የኢትዮጵያ ትወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 101/1996 ነው፡፡

2.7. በአዋጁ እና በደንቡ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

2.8. የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴ ማለት ከኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ልዩ ለዩ ጉዳዮችን በተመለከተ የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ አመራር የሚያቀርብ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ከአገልግሎቱ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡

2.9. በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

3.1. ይህ መመሪያ ለረጅም አመታት በአገራችን የፀና የመኖሪያ ፈቃድ፣ የጉዞ ሰነድ ሳይኖራቸው ወይም ኖሯቸው ሳያሳድሱ ሲኖሩ የነበሩ የራስ-ተፋሪያን አባላት ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለረጅም አመታት በአገራችን ሳይኖሩ በተጨባጭ ለአገራችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የማህበረሰቡ አባላት ይህንንም ሚኒስቴሩና አገልግሎቱ ሲያምኑበት ለኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ አገር ዜጎች የተሰጡ መብቶች እና ጥቅሞች እንዲያገኙ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ</u>

4. <u>ስለ መታወቂያ ካርድ</u>

በዋና መምሪያው በሚደረግ ማጣራት መሰረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ለሚያቀርብ ለረጅም አመታት በአገራችን መኖሩ የተረጋገጠ የራስ ተፈሪያን የማህበረሰቡ አባል የኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ ይሰጣዋል፡፡

5. <u>መብቶች እና ገደቦች</u>

5.1. በዚህ መመሪያ መሰረት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የተሰጣቸው የማህበረሰቡ አባላት የሚያገኙት መብቶች:-

ሀ. ወደ ኢትዮጵያ ለመግባትና ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየትም ሆነ ለመኖር የመግቢያ ቪዛና የመኖሪያ ፍቃድ እንዲኖረው አይጠየቅም፡፡

ለ. የስራ ፍቃድ እንዲያወጣ ሳይገደድ በዚህ አንቀ ፅ ንዑስ አንቀፅ 5.2 ከተዘረዘሩት የስራ መስኮች ውጪ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመስራት ይችላል፤

ሐ. አግባብ ባለው የጡረታ ህግ የውጭ ዜጎች የመብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚገድበው ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንበትም፤

መ. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ገደቦች አይመለከቱትም፡፡

ሠ. እንዳአገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር ከፈለገ በአገሪቱ የኢንቨስትመንት ህግ መሰረት ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተፈቀዱ የኢንቨስትመንት መስኮች መሳተፍ ይችላል፡፡

ረ. የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን በመጠቀም ረገድ በውጭ ዜጎች ላይ በህግ፣በመመሪያ ወይም በአሰራር ልምድ የተጣሉ ገደቦችና የሚደረጉ ልዩነቶች አይመለከቱትም፡፡

5.2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ደንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበረሰቡ አባላት የሚከተሉት ገደቦች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡-

ሀ. በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብት አይኖረውም፡፡

ለ. በማናቸውም የሀገር መከላከያ፣ የሀገር ደህንነት ወይም በውጭ ጉዳይና መሰል የፖለቲካ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በመደበኛነት ተቀጥሮ መስረት አይችልም፡፡

## 6. <u>መታወቂያ ካርዱ ስለሚሰጥበት ሁኔታ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት አስፈላጊው ማጣራት ተከናውኖ እና የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟላ የማህበረሰቡ አባል መታወቂያ ካርዱን ለማግኘት የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

6.1. ቢያንስ ለ6 ወር አገልግሎቱ የፀና የጉዞ ሰነድ፤ ወይም

6.2. የልደት ሰርተፍኬት ዋናውን ከሁለት ኮፒ ጋር፤ ወይም

6.3. እንደ አግባብነቱ በአገራችን ለረጅም ዓመታት መኖሩን ሊያስረዳ የሚችል በኢትዮጵያ የመንግስት አካል የተሰጠ የንብረት ባለቤትነት፣የግብርና፣ የኮሚዩኒቲ ተሳትፎ የሰነድ ማስረጃ እና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ማቅረብ፤

6.4. የሚያቀርበው የሰነድ ማስረጃ ከሌለ በአካባቢው ነዋሪ ለመሆኑ የሚያስረዱ ሶስት የሰው ምስክሮች፤

6.5. በቅርብ ጊዜ የተነሳውና ሙሉ ፊቱን የሚያሳይ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ

7. <u>ስለ አገልግሎት ክፍያ</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት መታወቂያ ካርድ የሚሰጣቸው የማህበረሰቡ አባል በደንቡ አንቀጽ አምስት መሰረት መታወቂያ ካርዱን ለማግኘት የሚጠየቀውን የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

8. <u>መታወቂያ ካርዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠ የመታወቂያ ካርድ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ ለአምስት ዓመታት የፀና ይሆናል፡፡

9. <u>ስለውዝፍ አገልግሎት ክፍያዎች</u>

1. አግባብ ባለው ሕግ ለመኖሪያ ፈቃድ እና ሌሎች አገልግሎቶች በአገራችን የሚኖሩ የውጭ አገር ዜጎች መከፈል ያለባቸው ክፍያዎችን በዚህ መመሪያ የመብት ተጠቃሚ የሚሆኑ የማህበረሰቡ አባላት አይከፍሉም፡፡
2. የማህበረሰቡ አባላት ከመኖሪያ ፈቃድና ሌሎች የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ጋር የነበሩባቸው ዕዳዎችና ውዝፍ ክፍያዎች በዚህ መመሪያ መሰረት ተሰርዘዋል፡፡

10. <u>በአፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ ውስብስብ ጉዳዮች</u>

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ በሚሆንበት ወቅት በመመሪያ 19/2007 ለተቋቋመው ቴክኒክ ኮሚቴ ቀርቦ ውሳኔ የሚያገኝ ይሆናል።

11. <u>የመታወቂያ ካርድ ስለመመለስ</u>

11.1 ማንኛውም መታወቂያ ካርድ የያዘ የማህበረሰቡ አባል በአዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀፅ 13 መሰረት በማናቸውም ጊዜና ምክንያት መታወቂያውን መመለስ ይችላል፡፡

11.2 መታወቂያውን ለመመለስ የሚፈልግ የማህበረሰቡ አባል የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 19/2007 መታወቂያ ካርድ ስለመመለስ የሚለው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12. <u>መታወቂያ ካርድ ስለመሰረዝበት ሁኔታ</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታዎች የሚደነግጉ በአዋጅና በደንቡ የተደነገገው በማህበረሰቡ አባላት ላይ እንደተጠበቁ ሆነው፡-

12.1 መታወቂያ የተገኘው ሌላ ሰው መስሎ ማቅረብ ወይም ስለራሱ ትክክለኛውን ነገር በመደበቅ ወይም የተሳሳተ ማስረጃ በማቅረብ ከሆነ፤

12.2. የመታወቂያው ባለቤት በሽብርተኛነት ተግባር ወይም ሰዎችን ወይም የተከለከሉ ዕፆችን ወይም የጦር መሳሪያዎች ወይም ገንዘብ በሕገ-ወጥ መንገድ በማዘዋወር ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

12.3. የመታወቂያው ባለቤት ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ላይ ያለ አገር ዜጋ ከሆነ ወይም ይህን አይነቱን አገር በፈቃደኝነት የሚረዳ ሰው ከሆነ፤

12.4. የመታወቂያ ባለቤት በሌላ አገር መንግስት በመደበኛ ውትድርና ወይም በደሕንነት ስራ ማገልገሉ ከተረጋገጠ፤

12.5. መታወቂውን ይዞ መቆየቱ ለህዝብና ለአገር ጥቅም እንዲሁም ለአገርና ለህዝብ ፀጥታና ደህንነት ተገቢ አለመሆኑ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

12.6. በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር 354/1995 መሰረት የአደገኛ ዕፅ ሱስ ተገዢ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም አደገኛ ወንጀለኛ መሆኑ ከታወቀ ወይም በወንጀል ህጉ መሰረት ከሀገር እንዲወጣ በፍርድ ቤት የተወሰነበት ወይም በወንጀል ህጉ ከአገር የሚያስወጣ ጥፋት የፈፀመ ለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት የማህበረሰቡ አባል ከሆነ፡፡

12.7. መታወቂያ ካርዱ የተሰረዘበት የራስ ተፈሪያን ማህበረሰብ የትዳር ጓደኛ መታወቂያ ካርድ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ ይሁንና እንዳይሰረዝበት አሳማኝና በቂ ምክንያት ያለው አመልካች ጥያቄውን በሚሲዮን ወይም በኢሚግሬሽን በኩል ለቴክኒክ ኮሚቴው ቀርቦ በበላይ አካላት ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

12.8. ጋብቻው በፍች ወይም በሞት ሲፈርስ የተሰጠው መታወቂያ ካርድ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ ጋብቻው በፍች ወይም በሞት ሲፈርስ መታወቂያ ካርዱን የያዘው ባለቤት በገባው ግዴታ መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካላሳወቀ መታወቂያ ካርዱ ሊሰረዝ ይችላል፡ ይሁንና እንዳይሰረዝበት አሳማኝና በቂ ምክንያት ያለው አመልካች ጥያቄውን በሚሲዮን ወይም በኢሚግሬሽን በኩል ለቴክኒክ ኮሚቴው ቀርቦ በበላይ አካላት ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

12.9. የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን በተውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 19/2009 መታወቂያ ካርድ ስለመሰረዝ የሚለው በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

13. <u>መመሪያውን ስለ ማሻሻል ወይም ስለ መለወጥ</u>

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት በጋራ በሚያቀርቡት ውሳኔ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡

14. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚሆነው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ቀን ሰኔ 2 ቀን 2009 ዓ.ም

ወርቅነህ ገበየሁ (ዶ/ር)
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር